Sept 7,2013

አጫጭር መንፈሳዊ መጻጽፎች(short devotional articles)

## ማለኮታዊ ገጠመኝ(holy encounter with God)

ባለፉት ዘመናት በጽሁፍ ላይ ያየናቸው ማለኮታዊ የሆኑ ጉብኝቶችና ገጠመኞች አሁንም በዚህ ዘመን በሚባ ሲከሰቱ ይስተዋላል፤ማለኮታዊ ጉብኝት ጊዜ ያለፈበት ጉዳይ አይደለም፡
ከጌታ ጋር አብዛኛውን ጊዜ የምንገናኘው ቃሉን ስናነብና ስጸልይም ቢሆንም አንዳንዴ እኛ ባለሰበነው መንገድ እራሱን ገልጦልን ህይወታችን እስከወዲያኛው ሊቀየር ይችላል፡፡እንደዚህ አይነት ክስተት ያልጠበቅነውና በእራሱ ጊዜ ራሱ ባቀደው ሰአት ስለሚሆን በፍጹም በህይወታችን ልንረሳው አንችልም፡እንዳልኩት ይህን ገጠመኝ እኛ ልናቅደውና በፈቃዳችን ልንለማምደው አንችልም፡ከእኛ የሚጠበቀው መንፈሳዊ ጆሮአችንንና አይኖቻችንን ከፍተን ለመቀበል ንቁ መሆን ነው፡
ማለኮታዊ ገጠመኞች ወደ ህይወታችን እንዳይመጡ ምን ከለከለን ?

- ልባችን በብዙ ነገር ተይዟል
- ጆሮአችን በሌሎች በሚጮሁ ነገሮች ተደፍኗል
- ጠበቅ አድርገን የጌታን ፊት ሚፈልግ አቃተን

ማለኮታዊ ገጠመኝ(holy encounter) ሲመጣ ምንድነው የሚሆነው ?

- አንድ የእግዚአብሄር ሰው እንዲህ ብለዋል፡-

<<an encounter with God opens our eyes to recognize His unapproachable superiority>>

- ህልውናው በሚገርም ሁኔታ ይታወቀናል
- ያለሱ የማንረባ ሰዎች መሆናችን እናውቃለን
- የእግዚአብሄርን መሀሪነት እንገነዘባለን
- በተግባር ደረጃ ታዛዦች እንሆናለን

በኢዮብ መጽሀፍ ላይ ኢዮብ ወደ መጀመሪያ አካባቢ የነበረው መንፈሳዊ አቋም በሚቀጥለው ጥቅስ ተንጸባርቋል፡፡እንዲህ የሚል ነው፡-<<ጽድቄን እይዛለሁ እርሱንም አልተወም ከቀኖቼ ሁሉ ስለ አንዱ ልቤ አይዘልፈኝም>>፡፡ከጓደኞቹ ጋር በርከት ያለ ምእራፎች ሲከራከር ከቆየ በኋላ እግዚአብሄር ክብሩንና ማንነቱን በሚባው መንገድ ሲገልጽለት ከመጀመሪያው አቋሙ እጅግ የሚለይና የልብ ማስበር የታየበት ምላሽ ነበር የነበረው፡እንዲህ በማለት ፡-<<መስማትን በጆሮዬ በመስማት ሰምቼ ነበር አሁን ግን አይኔ አየችህ ስለዚህ እራሴን እንቃለሁ፤በአፈርና በአመድ ላይ ተቀምጬእጸጸታለሁ>> እጅግ የሚገርም እና ለጌታ የተንበረከከ ሰው ቋንቋ ነው፡ለዚህ ምላሽና መንበርከክ ያበቃው የእግዚአብሄርን ታላቅነትና ሁሉን ቻይነቱን በመንፈሱ ሚቱ ነው፡
እግዚአብሄርን በግርማውና በክብሩ ማየት አስደንጋጭና አስፈሪ ልምምድ ቢሆንን በሕይወታችን የማንረሳውና በውስጣችን ታትሞ የሚቀር ስለሚሆን ለመንፈሳዊ እርምጃችን እጅግ ጠቃሚ ነው፡አንድ የእግዚአብሄር ሰው በጻፉት መጽሃፋቸው ላይ  የእግዚአብሄር ሰዎች ጌታን ለማገልገል ሲነሱ እንዲህ አይነት ገጠመኝ (traumatic experience) ቢኖራቸው ሚላካም ነው ይላሉ፡፡
እንዲህ አይነት ገጠመኝ(holy encounter) በህይወታችን ትልልቅ ለውጦችን ያመጣል ፡፡ለምሳሌ፡-

- የልብ ማስበር
- ጥልቅ ንስሀ

- በቃላት መናገር የማይቻል ደስታ

- ታዛኝሰት

ኢሳ 6፤1-8 ላይ የተከሰተው ነገር በኢዮብ ላይ ከተከሰተው ሁኔታ ጋር በለያይም የሚያመሳስላቸው ነገር ግን ላዩት ነገር የሰጡት ምላሽ ነው፡፡በሁለቱም ህይወት የልብ ማሰበር ይታያል፡፡ነቢዩ ኢሳያስ እግዚአብሄርን በሚገርም ግርማና አስፈሪ ክብር ሲያይ እንዲህ አለ፡-<<ከንፈሮቼ የረከሱብኝ ሰው በመሆኔ ከንፈሮቻቸውም በረከሱባቸው ህዝብ መካከል በመቀመጤ አይኖቼ ጌታ ንጉሱን እግዚአብሄርን ስለ አዩ ጠፍቻለሁና ወዮልኝ >>

በእኛም ህይወት እንዲህ ነው የሚሆነው፡፡የጌታን ግርማ፣ሀያልነት፣ቅድስናና ክብሩን እስከናይ ድረስ ሰዎችን አብጠልጣይ፣ትእቢተኛ፣ከሩ፣አትንኩኝ ባይ፣ተናጋሪ፣ከሳሽና ግትር ነን፡፡እርሱን በክብሩ ስናየው ግን ነገሮች 360 ዲግሪ ይቀየራሉ፡፡

ከላይ የተገለጸው ማለኮታዊ ገጠመኝ(holy encounter) ሲያገኘን በሚደረሳ ህይወታችንን ስለሚለወጥ እንደ እዮብ <<እራሴን እንቃለሁ>> ወይም እንደ ነቢዩ ኢሳያስ <<ጠፍቻለሁ ወዮልኝ>> እንላለን እንጂ ሌላ ቋንቋ አይኖረንም፡፡ስለዚህ ይህንን ማለል ቅዱስ ገጠመኝ (holy encounter) እንዲኖረን በጌታ ፊት እንወደቅ!

## ከልብህ ሀዘንን አርቅ

ወደ ስምንት አመት ገደማ ይሆናል፡፡በአንድ ከፍ ያለ የልብ ስብራት ወስጥ ሆኜ መቆዘም አብዝቼ ነበር፡፡ሀዘኔ ከበድ ያለ ስለነበር ከሰው ጋር መገናኘትና ማውራት አስጠልቶኝ ሁሉ ነበር፡፡በዛ ሁኔታ ወስጥ ሳለሁ የጌታ መንፈስ ደረሰልኝና አንድ ነገር አበረልኝ፡፡እርሱም ይህንን ያለሁበትን ሁኔታ የሚገፍ ሀላፊነት የኔ እንደሆነ በቃሉ ብርሀን ተገነዝብኩ፡የበራለኝ ቃል የሚገኘው መክብብ 11፡10 ላይ ያለ ቃል ሲሆን እንዲህ ይነበባል፡-<<ከልብህ ሀዘንን አርቅ>>

ይህ ቃል የበራልኝ ቀን በሚገርም ሁኔታ ነበር ወስጤ በግርምት የተሞላው፡፡አዝኜ የሰይጣንና የአጋንንቱ መጫወቻ ሆኜ እያላዘንሁ መቀመጥ እንደሌለብኝ በሚገባ ገባኝ፡፡ከዛም ከነበርሁበት ሁኔታ ለመውጣት ጌታ ጠንከር ያሉ ጸሎቶችን በማያዝ ትግል መጀመር እንዳለብኝ አማለከተኝ፡፡

ባጋጣሚ የምኖርበት ቤት አጠገብ አንድ የማሪተ ክርስቶስ አጥቢያ ቤ/ክ ነበርና እዚያ በፈረቃ ግቢውን የሚጠብቁትን ሰራተኞች እያስፈቀድሁ በጣም ረጅም ሰአታት ባዶ አዳራሽ ወስጥ ሜጮ ጀመርሁ፡፡መጀመሪያ ይህንን ትግል ስጀምር ልክ ግምብ የመግፋት ያህል ይሰማኝ ነበር፡፡የሚሰማኝ ስሜት ሳይበግረኝ በጸሎት መስገስ ጀመርሁ፡፡በመሀል አንዳንዴ ካለሁበት ሁኔታ ጋር የሚዛመድ የመጽሀፍ ቅዱስ ክፍሎችን እያጠናሁና እያሰላሰልሁ ከዚያ ደግሞ ቀጥዬ በመቃተትና የጌታ መንፈስ እንዲረዳኝ በመጮኽን ሳልፈወስ ከምሸጌ ላልወጣ ለራሴ ቃል ገባሁ፡፡ለተወሰኑ ቀናት እንዲህ ባለ ሁኔታ ካሳለፍኩ በኋላ ሁኔታው ሁሉ ተገልብጦ ሰላምና ደስታ በሚቋርጥ ሁኔታ በልቤ ወስጥ ይፈስ ጀመር፡፡ዝሜሬ፣ አምልኮ፣ስግደት ፣ወዳሴ ወዘተ በሕይወቴ ተትረፈረፈ፡፡እየጸለይኩ ወዬ፤ስለጌታ አወሮቼ ፤አማስግኜ ወዘተ አልረካም ነበር፡፡እዚህ ምድር ላይ ሁሉ የምኖር አልመሰለኝ ሁሉ አለ፡፡የእግዚአብሄር ህልወና በሚገርም ሁኔታ እላዬ ላይ ነበር፡፡ብቻዬን ሆኜ ማንም ሳያወራኝ ሁሉ ሳቅ ያስፈነድቀኝ እንደነበር ሁሉ ትዝ ይለኛል፡፡የነበርኩበትን ሁኔታ በቃላት መግለጽ ያዳግተኛል፡፡ወገኖቼ ልብ በሉ እያጋነንሁ አይደለም እውነተኛ ነገር ነው የምናገረው፡፡ክርስትና ዝም ብሎ ስርአት እንዳልሆነ በህይወቴ አይቻለሁ፡፡ጌታ ቅርብ ነው የሚለው ቃል የታመነ ነው፡፡

ኢሳ 35፡10 ላይ የነበርኩበትን ሁኔታ የሚገልጸው ይመስለኛል፡፡እንዲህ ይነበባል፡- <<እግዚአብሄርም የተቤዣቸው ይመለሳሉ እየዘመሩም ወደ ጽዮን ይመጣሉ የዘላለም ደስታ በራሳቸው ላይ ይሆናል ሀሴትንና ደስታን ያገኛሉ ሀዘንና ትካዜም ይሸሻሉ>>አዎ ያ ሁሉ ሀዘንና ትካዜ የት እንደገባ እስገሚገርመኝ ድረስ በሀሴት ተጥለቀለቅሁ፡፡ለዚህ ነው ኢሳ 10፡27 <<በዚያም ቀን ሸክሙ ከጫንቃህ ቀንበሩም ከአንገትህ ይወርዳል ቀንበሩም ከወፍረት የተነሳ ይሰበራል>>የሚለው፡፡ጠበቅ ያሉ ጸሎቶችን ስናበዛ የሀይል መንፈስ በወስጣችን እየጨመረ ስለሚሄድ ማንኛውንም አዚም ለማሰበር የምንችልበትን አቅምና ጉልበት እናገኛለን፡፡

ይህን የምናገረው በቀለም ደረጃ ሳይሆን በህይወቴ ዳስሼ ስላየሁት ነው፡፡በጽኑነት ከልብ ሆነንና በቀጣይነት ሳንታክት በምንጸልየው ጸሎት ብዙ ድንቅ ማለኮታዊ ነገሮችን እናያለን፡፡ስለዚህ ከነካ ነካ የጸሎት ሕይወት ጌታ ወደ ጠለቀ ልምምድ እንዲከተን ሳንታክት ፊቱን እንሻ፡፡እንዲህ ብናደርግ ያስደንቀናል፡፡ስሙ ለዘላለም የተባረከ ይሁን!

ስሜ በቀለ በላቸው (ዶ/ር) ይባላል በጌትስበርግ ሜሪላንድ አካባቢ የምኖር ስሆን በመንፈሳዊ ስነ-ጽሁፍና መጽሀፍ ቅዱስን በማስተማር ጌታን አገለግላለሁ፡በጽሁፎቼ ላይ አስተያየት ለማስጠትና ከኔ ጋር የጌታን ስራ ለማስራት ለምታስቡ ሰዎች በሚቀጥለው አድራሻ ልታገኙኝ ትችላላችሁ፡

ኢ-ሜይል አድራሻ፡-beke_abay@yahoo.com

ስልክ ቁጥር፡-240-507-9148/240-330-5004

ጌታ ህይወታችሁን ይባርክ!